# ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው፦

# በ IDEA እና በምዕራፍ 3323 ሥር ያሉትን መብቶች ከኦቲዝም ነፃ የትምህርት ዕድል ፕሮግራም ጋር ንጽጽር

| IDEA እና ምዕራፍ 3323 | የኦቲዝም ነፃ የትምህርት ዕድል ፕሮግራም |
|---|---|
| አንድ የመንግስት ትምህርት ቤት አውራጃ ለአካል ጉዳተኞች ተማሪዎች **ነጻ ተገቢ የመንግሥት ትምህርት (FAPE)** ማቅረብ አለበት። **ነጻ ተገቢ የመንግሥት ትምህርት** የሚከተሉትን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፦<br>• ያለምንም ወጪ ይሰጣሉ፤<br>• የOhio የትምህርት እና የሠራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) መስፈርቶችን ያሟላሉ፤<br>• ተገቢውን የቅድመ ትምህርት ቤት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያካትታሉ፤ እና<br>• የOhio የIEP መስፈርቶችን በሚያሟላ IEP መሠረት ይሰጣሉ።<br>ልዩ ትምህርት የአካል ጉዳተኛ ልጅን ፍላጎት ለማሟላት በልዩ ሁኔታ መመሪያ የተዘጋጀ ትምህርት ነው።<br><br>የተዛማጅ አገልግሎቶች ምሳሌዎች ትራንስፖርት፣ የንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ አገልግሎቶች፣ የኦዲዮሎጂ አገልግሎቶች፣ የትርጉም አገልግሎቶች፣ የአካል እና የሙያ ቴራፒ፣ መዝናኛ እና የምክር አገልግሎቶችን ያካትታል። | በኦቲዝም ነፃ የትምህርት ዕድል ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፍ ልጅ በግል የተቀመጠ ተማሪ ነው እናም **ለFAPE መብት የለውም**። |
| FAPE ለወላጆች ያለ ምንም ወጪ መሰጠት አለበት። | አንድ ተሳታፊ ተማሪ በተመዘገበ የግል አቅራቢ ወይም አማራጭ የሕዝብ አቅራቢ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ለመክፈል እስከ $32,445 ነፃ የትምህርት ዕድል ይቀበላል። የፕሮግራሙ ወጪ ከነፃ የትምህርት ዕድሉ የበለጠ ከሆነ ወላጆቹ ኃላፊነት አለባቸው። |
| አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት አውራጃ በአውራጃው ውስጥ የግል ፕሮግራሞችን የሚከታተሉ ተማሪዎችን ጨምሮ የአካል ጉዳተኝነት የተጠረጠሩ ተማሪዎችን **መገምገም** ይጠበቅበታል። | አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት አውራጃ በአውራጃው ውስጥ የግል ፕሮግራሞችን የሚከታተሉ ተማሪዎችን ጨምሮ የአካል ጉዳተኝነት የተጠረጠሩ ተማሪዎችን **መገምገም** ይጠበቅበታል። |
| አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት አውራጃ አንድ ተማሪ በ IDEA መሠረት ብቁ እንደሆነ ከተወሰነ በኋላ **የመጀመሪያውን IEP** ያዘጋጃል። | አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት አውራጃ አንድ ተማሪ በ IDEA መሠረት ብቁ እንደሆነ ከተወሰነ በኋላ **የመጀመሪያውን IEP** ያዘጋጃል።<br>አንድ ተማሪ የመጀመሪያውን IEP እስኪያጠናቅቅ ድረስ ለነፃ የትምህርት ዕድል ብቁ አይደለም። |
| **አገልግሎቶችን ማቅረብ።** የትምህርት ቤቱ አውራጃ በIEP ውስጥ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች በሙሉ ማቅረብ ይጠበቅበታል። | **አገልግሎቶችን ማቅረብ።** የነፃ ትምህርት ዕድሉ ጥቅም ላይ የሚውለው የልጁን IEP ተግባራዊ በሚያደርግ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ላይ ለመገኘት ወጪ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ የነፃ ትምህርት ዕድል አቅራቢው በ IEP ላይ የተዘረዘሩትን ሁሉንም አገልግሎቶች እንዲያቀርብ ምንም መስፈርት የለም። |
| **የIEP ዓመታዊ ግምገማ**። በየዓመቱ ወይም አስፈላጊ ከሆነ በተደጋጋሚ የIEP ቡድን IEPን ይገመግማል። | **የ IEP ዓመታዊ ግምገማ።** በየዓመቱ የ IEP ቡድን IEPን ይገመግማል። |



Department of Education & Workforce

| | |
|---|---|
| **ዳግም ግምገማ**። ወላጅ እና አውራጃው እንደገና መገምገም አስፈላጊ እንዳልሆነ ካልተስማሙ በስተቀር፤ የትምህርት ቤቱ አውራጃ ተማሪውን በየሦስት ዓመቱ እንደገና ይገመግመዋል። | **ዳግም ግምገማ**። ወላጅ እና አውራጃው እንደገና መገምገም አስፈላጊ እንዳልሆነ ካልተስማሙ በስተቀር፤ የትምህርት ቤቱ አውራጃ ተማሪውን በየሦስት ዓመቱ እንደገና ይገመግመዋል። |
| **ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ። የትምህርት ቤት አውራጃ ግምገማውን ለመከላከል ተገቢውን የችሎት ሂደት ካልጀመረ በስተቀር** አንድ ወላጅ ከግምገማው ጋር የማይስማማ ከሆነ ወላጅ በሕዝብ ወጪ የ IEE መብት አለው። | **ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ። የትምህርት ቤት አውራጃ ግምገማውን ለመከላከል ተገቢውን የችሎት ሂደት ካልጀመረ በስተቀር** አንድ ወላጅ ከግምገማው ጋር የማይስማማ ከሆነ ወላጅ በሕዝብ ወጪ የ IEE መብት አለው። |
| **ሽምግልና**። ODE በIDEA ሥር የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ያለ ምንም ክፍያ ሽምግልናን ይሰጣል። | **ሽምግልና**። ODE በወላጆች እና በሕዝባዊ ትምህርት ቤት አውራጃ መካከል የIEPዎች እድገት ዙሪያ የሚነሡ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሽምግልና ይሰጣል፣ **ግን በወላጆች እና በነፃ ትምህርት ዕድል አቅራቢዎች መካከል ላሉ አለመግባባቶች አደለም።** |
| **የተመቻቸ IEPዎች**። ODE የ IEPዎች እድገት ውስጥ ለመርዳት አስተባባሪዎችን ያቀርባል፣ ከተጠየቀ። | **የተመቻቸ IEPዎች**። ODE የ IEPዎች እድገት ውስጥ ለመርዳት አስተባባሪዎችን ያቀርባል፣ ከተጠየቀ። |
| **ቅሬታዎች**። ODE አንድ የትምህርት ቤት አውራጃ የመኖሪያ ቤት የ IDEA ወይም የOhio አስተዳደራዊ ኮድ 3301-51-05 ጥሷል የሚሉ የጽሑፍ ቅሬታዎችን ይመረምራል። | **ቅሬታዎች**። ODE የመኖሪያ ትምህርት ቤት አውራጃ የ IDEA ወይም የOhio አስተዳደራዊ ኮድ መስፈርትን እንደጣሰ የጽሑፍ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ነገር ግን የአንድ አቅራቢ የ IEP አፈጻጸምን የሚመለከቱ ወይም ልጁ FAPE አግኝቶ እንደሆነ ያሉ ክሶችን አይመረምሩም።<br><br>ODE አንድ አቅራቢ በኦቲዝም የነፃ የትምህርት ዕድል ህጎች ወይም ደንቦች ውስጥ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን እንደጣሰ የጽሑፍ ቅሬታዎችን ይመረምራል። |
| **የችሎት ሂደት ጥያቄዎች**። ወላጆች እና ተማሪዎች የአካል ጉዳተኛ ልጅን ከመለየት፣ ከመገምገም ወይም ከትምህርት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ለመቃወም ወይም ለልጁ FAPE ለመስጠት አስተዳደራዊ አሰራርን ለመጀመር የችሎት ሂደት ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው። | **የችሎት ሂደት ጥያቄዎች**። አንድ ወላጅ ወይም ተማሪ የልጁን መለያ ወይም ግምገማ በተመለከተ ውሳኔዎችን በመቃወም ተገቢውን ሂደት ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል ፣ ነገር ግን በግል አቅራቢው ከሚሰጡት አገልግሎቶች ወይም ልጁ በነፃ የትምህርት ዕድል ፕሮግራም ውስጥ በሚመዘገብበት ጊዜ FAPE አግኝቶ እንደሆነ ላሉ (ለተዛመዱ) የችሎት ሂደት ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም። |
| **የመገለጫ ቁርጥ ውሳኔ**። አንድ የመንግስት ትምህርት ቤት አውራጃ የአካል ጉዳተኛ የሆነ ተማሪ የተማሪ ባህሪ ደንብ በመጣሱ ምክንያት አሁን ካለው/ካለችው የትምህርት መስክ ለተራዘመ ጊዜ ሲወገድ የመገለጫ ማረጋገጫ ግምገማ ያካሂዳል። የIEP ቡድን ይህንን ግምገማ የሚያካሂደው የተማሪው የአካል ጉዳት መገለጫ መሆኑን ወይም የሕዝብ ትምህርት ቤት አውራጃ የIEPን ተግባራዊ ባለማድረጉ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ለመወሰን ነው። ቡድኑ ባህሪው መገለጫ መሆኑን ካረጋገጠ ተግባራዊ የባህሪ ግምገማ (FBA) ማካሄድ እና የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ (BIP) መፍጠር ወይም የተማሪውን ነባር BIP መገምገም እና መለወጥ አለባቸው። | **የመገለጫ ቁርጥ ውሳኔ**። ተማሪዎች በግል አቅራቢው የዲሲፕሊን ፖሊሲዎች ተገዢ ናቸው። ተማሪው የአቅራቢውን የሥነ ምግባር ደንብ በመጣሱ ሊታገድ ወይም ሊባረር ይችላል። |

*የኦሃዮ የትምህርት እና የሠራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በዜግነት፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት ወይም በዘር መሠረት አድልዎ አያደርግም። የኦሃዮ የትምህርት እና የሠራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) እኩል እድል የሚሰጥ አሰሪ እና የADA አገልግሎቶች አቅራቢ ነው። የመምሪያው አድልዎ-አልባነት ማስታወቂያ ለሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ተፈጻሚ ይሆናል።*
*የመምሪያውን የአካል ጉዳተኝነት መድልዎ ፖሊሲ እና የአካል ጉዳተኝነት መድልዎ ፖሊሲ ቅሬታ አሠራር ይመልከቱ።*
*ስለ አድልዎ አለማድረግ ማስታወቂያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በአካባቢዎ ያለውን ጽሕፈት ቤት አድራሻ እና የስልክ ቁጥር ለማግኘት ocrcas.ed.gov/contact-ocr ይጎብኙ ወይም 1-800-421-3481 ላይ ይደውሉ።*



Department of Education & Workforce